የገቢዎች ሚኒስቴር
Ministry of Revenues

# ገቢያችን ህልውናችን

15ኛ ዓመት | ቁጥር 172 | ሚያዚያ 2016 ዓ.ም | በነፃ የሚታደል

በውስጥ ገፃችን



<<ግብርን በታማኝነት መክፈል በርካታ ጠቀሜታዎች አሉት>>
ወ/ሮ ማህሌት አምዴ
ገጽ 3

በሚሊዮን የሚቆጠር ብር ወጪ ለማዳን
ገጽ 5

ገቢዎችን የተመለከቱ ወቅታዊ፣ ትኩስ እና የተሟሉ መረጃዎችን ለማግኘት፡- በማህበራዊ መገናኛ ዘዴዎቻችን ይጎብኙ

1. በድረ ገጽ፡- www.mor.gov.e
2. በቴሌግራም፡- https://t.me/MoREthiopiaOfficial/169
3. በፌስቡክ፡- https://www.facebook.com/ERCA.info or ministryofrevenuesofethiopia /የገቢዎች ሚኒስቴር/
4. በዩትዩብ፡- https://www.youtube.com/@ministryofrevenuesofethiop1677/videos Or ministryofrevenuesofethiopia
5. በቲክቶክ አጫጭር መረጃ https://vm.tiktok.com/ZM61hdty2/

በቴሌቪዥን ፕሮግራሞቻችን

6. ዋልታ ቴሌቪዥን ሰኞ ማታ ከ 2፡30 ጀምሮ
7. ፋና ቴሌቪዥን ሐሙስ ማታ ከ2፡00 ዜና በኃላ
8. ኢቲዮጵያ ቴሌቪዥን /ኢ.ቢ.ሲ/ ቅዳሜ ማታ ከ2፡00 ዜና በኋላ

በሬድዮ ፕሮግራሞቻችን

9. ፋና ኤፍ ኤም ሬድዮ 98.1 ሐሙስ ማታ ከ2፡30 ጀምሮ
10. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሬድዮ 93.1 ማክሰኞ ጠዋት ከ2፡30 ጀምሮ
11. በወርሃዊ ጋዜጣችን፡- ገቢያችን ህልውናችን

# ማጉፋሊ እና ሙዚቃ ምን አገናኛቸው?





ታንዛኒያን ለአስር ዓመታት በፕሬዚዳንትነት መርተዋት የነበሩት ጆን ማጉፋሊ የሀገራቸው ራፐር ናይ ዋ ሚቴጎ እ.ኤ.አ. በ2017 ወደ አማርኛ ሲተረጎም፣

«እስኪ ንገሪኝ አገሬ፣
ነጻነት አለ ወይ በሰፈሬ?
ያሻኝን ብዘፍን ጉራማይሌ
አገኘው ይሆን ራሴን ከርቸሌ?» የሚል ሀሳብ ያለውን ዘፈን ስለዘፈነባቸው

ሙዚቃውን በለቀቀ በሰዓታት ውስጥ እራሱን ያገኘው እስር ቤት ነበር።

ፕሬዝዳንቱ ተቺያቸው የሆነውን ሙዚቀኛ ከእስር ካስፈቱት ከአንድ ቀን በኋላ፣ «ስለ ግብር አጭበርባሪዎች ሙዚቃ ሥራልኝ» ብለው መከሩት። ፕሬዚዳንቱ ይህን ያሉት ግብር አጭበርባሪዎች በጣም ያናድዷቸው ስለነበር ነው።

ማጉፋሊ እና ሙዚቃ ... ወደ ገጽ 5 ዞሯል

# የጊዜ ነገር...






«የተቀበረች ሀቅ...ቋጥኝ የተጫናት፣
አራሙቻ ውሸት...አረም የሸፈናት፣
ቋጥኙን ፈልቅቆ...አረሙን አርሞ፣
ያወጣት ጊዜ ነው...ለጠበቀ ቆሞ»

የጊዜ ነገር... ወደ ገጽ 2 ዞሯል

# ርዕሰ አንቀጽ




## ተጠያቂነትም፣ ውጤት አልባነትም እንዳይኖር...

ሕግን አለማወቅ ከተጠያቂነት ስለማያድን ሰዎች ባለማወቃቸው ተጠያቂ እንዳይሆኑ መጣር ይጠበቅባቸዋል፡፡ ከዚህ አኳያ ግብር ከፋዮቻችን የታክስ እና የጉምሩክ ሕጎችን አለማወቃቸው ችግር እንዳይፈጥርባቸው ሕጎችን፣ መመሪያዎችን እና የአሰራር ስርዓቶችን ሲፈልጉ በቀላሉ እንደማያገኙ ሚኒስቴር መ/ቤታችንን ሲወቅሱ ይሰማ ነበር፡፡ ይህ የሆነው ተደራሽ መሆን የሚገባቸውን መረጃዎች ለማድረስ የተለያዩ አስቸጋሪ ሁኔታዎች ስለነበሩ ነው፡፡

ከነዚህ መካከል ከአዋጆቹ እስከ መመሪያዎቹ ያሉ የታክስ እና የጉምሩክ ሕጎች በነጋሪት ጋዜጣም፣ በጥራዝም ሆነ በተለያዩ የህትመት ውጤቶች ቢታተሙም ለማሰራጨት ሲታሰብ ወጪያቸው ስለሚበዛ የቅጂ ብዛታቸው የተፈለገውን ያህል አለመሆን ተጠቃሽ ነው፡፡

ያን ለማስቀረት በዚህ ዘመን እየተሠራበት ያለው መረጃዎችን በቴክኖሎጂ በመታገዝ ሶፍት ኮፒው ተደራሽ እንዲሆን ማሰራጨት እና ሰነዶቹ ላይ የሰፈሩትን ሀሳቦች ላይ ለግብር ከፋዮች ስልጠና መስጠት ነው፡፡ ከዚህ አኳያ የገቢዎች ሚኒስቴር እና ጉምሩክ ኮሚሽን ታክስ እና ጉምሩክ ነክ መረጃዎችን የተለያዩ መረጃ መስጫ መንገዶችን በመጠቀም በማሰራጨት ላይ ይገኛሉ፡፡

በዚህን ሕግ ነክ መረጃዎች ግብር ከፋዮች ይበልጥ ሊረዱት በሚችሉት አቀራረብ በጋዜጦች፣ በመጽሔቶች እና በመጻሕፍት እንዲሁም በብሮሸሮች እና በቡክሌቶች በማሳተም በተቻለ መጠን ለማዳረስ እየሠራ ነው፡፡ ከዚህ ሌላ ሰነዶቹ ያሰፈሯቸውን ሀሳቦች በማሳጠር በሬዲዮ እና በቴሌቪዥን ከማቅረብ ባሻገር የዩቲዩብ፣ የቲክቶክ የፌስቡክ እና የቴሌግራም ገጾችን በመጠቀም መረጃዎች እንዲደርሱ እየተደረገ ነው፡፡ እነዚህ ሰነዶች ሙሉ በሙሉ በተቋሙ ዌብሳይት ገጽ ላይም የተጫኑ በመሆናቸው እንዲነበቡ እየተደረገ ይገኛል፡፡

ሌላው፤ በሚኒስቴሩ እና በኮሚሽኑ በተቋቋሙት የትምህርት ክፍሎች አማካኝነት በልዩ ልዩ ጉዳዮች ላይ በመላ ሀገራችን ለሚገኙ ደንበኞች ስልጠና እየተሰጠ ይገኛል፡፡ ለዚህ ሲባል በሞጁል ደረጃ የተዘጋጁ ሰነዶች የተሰራጩ ሲሆን ከስልጠናው በኋላ የምዘና ፈተና ወጥቶ መጨረሻ ላይ በሰርቲፊኬት እየተጠናቀቀ ነው፡፡ በዚህ ረገድ የግብር ከፋዮች ፍላጎት ከጊዜ ወደጊዜ እየጨመረ በመሆኑ ድርጅቶች ለባለሙያዎቻቸው ጭምር ስልጠና እንዲሰጥላቸው እስከመጠየቅ ደርሰዋል፡፡

የነዚህ ሁሉ ድምር ውጤት የተለያዩ የንግድ ስራዎች እና ሌሎች የገቢ ዘርፎች በልምድ ብቻ ከሚመሩ በእውቀትም እንዲዳብሩ ማስቻል ነው፡፡ ከዚህ ባሻገር ደግሞ ምንም እንኳን ግብር ከፋዮች አውቀውም ሆነ ሳያውቁ የፈጸሟቸው ስህተቶች ከተጠያቂነት ባያድናቸውም ‹‹ታሞ ከመማቀቅ፤ አስቀድሞ መጠንቀቅ›› እንደሚባለው አሠራሮችን አውቆ እና አዘምኖ መሥራት ውጤታማነትን ከማሳደግ ባሻገር ስህተቶች ውስጥ ላለመግባት ያግዛል፡፡ ስለዚህ፤ ፍላጎቱ ያለው ሁሉ በፈለገው አማራጭ የሚፈልገውን መረጃ ማግኘት እንደሚችል፤ ተቋማችን ማሻሻል የሚገባቸው አሠራሮች ካሉም ከላይ በጠተቀሱት አማራጮች መጠቆም እንደሚገባቸው እናሳስባለን፡፡

ገቢያችን ህልውናችን፤ በገቢዎች ሚኒስቴር የኮምዩኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት
የሚዘጋጅ ወርሃዊ ጋዜጣ
የኤዲቶሪያል ቦርድ አባላት፡- አቶ አካሉ ጴጥሮስ ሰብሳቢ
አቶ እስክንድር መርሐጽድቅ አባል
አቶ ፀጥአርጋቸው ንጋቱ አባል

ዋና አዘጋጅ፡- ሰሎሞን ወርቁ
አዘጋጆች፡- ሺመልስ ሲሳይ
እታገኘ አቦሰጥ

ጸሐፊና ሌይአውት ዲዛይነር፡- ብርሃኔ ደመቀ
ፎቶግራፈር፡- ክፍሌ አዳፍሬ፣ እስካለም ሰፊው እና የትናየት እንዳያፍሩ

አድራሻ፡- ስልክ 11-6-17-84-90 ኮድ 8490 ፖ.ሣ.ቁ 2559
ዌብሳይት፡- www.mor.gov.et ኢሜል ethioerca@Gmail.com
ፌስቡክ Ministry of revenues of Ethiopia

ስታክስ እና ስጉምሩክ ጉዳዮች መረጃ ነጻ ስልክ፡- 8199

# የጊዜ ነገር...

ከገጽ 1 የዞረ



‹‹የምድራችን ትልቁ ጀግና ጊዜ ነው፡፡ ጊዜን ማሸነፍ ባይታሰብም በጊዜ የሠራ ግን ሀገሩን እና እራሱን ከመጥቀም አልፎ ለትውልድም ቅርስ ያቆያል››

ይህን ያለው በጉምሩክ ኮሚሽን በአሽከርካሪነት የሚሠራው ወጣት ሳምሶን ግርማ ነው፡፡ ሳምሶን ይህን ሲነግረን በመግቢያችን ያሰፈርነውን የድምጻዊት ሐመልማል ታሪክ ቀያሪ ስለሆነው "ጊዜ" የተቀኘችው ሙዚቃ ታወሰን፡፡

ሊጠናቀቅ ጫፍ የደረሰው የሕዳሴ ግድብ የዛሬ 13 ዓመት ከመጀመሩ በፊት በየዘመናቱ ሀገራችንን የመሩት መንግሥታት ባይሠሩትም ዕቅድ እንደነበራቸው፤ ቢያንስ የዓባይ ጉዳይ ቁጭት ውስጥ እንደከተታቸው በሙዚቃ ውስጥ ይገልጹት ነበር፡፡ ተግባራዊ ያልሆነበት ዋናው ምክንያት የሱዳን እና የግብፅ ጫና ማሳደር ተጠቃሽ ነው፡፡ ሌላው በተለያዩ ጫናዎች መነሻነት የገንዘብ አቅም አለመኖር ነው፡፡ ይህን መብት እና እውነት የጫና ፈጣሪዎቹ ውሸት በአረም ሸፍኖት ቢያቆየውም ጊዜ ጀግናው በደፋር ልጆቹ ትንሳኤው ላይ እንዳደረሰው ይህ የሙዚቃ ስንኝ በትክክል ገልጾታል፡፡

አስተያየቱን የጠየቅነው ሳምሶንም ያስቀመጠው የጊዜ ጉዳይም በግድቡ ታሪክ ተሠርቶበት ለትውልድ ቅርስ ሆኖ እንደሚቀመጥ አመልካችነቱን አጉልቶታል፡፡ ምክንያቱም፤ ግድቡ ሲጀመር በነበረው ሕዝባዊ ንቅናቄ ላይ ተናግሮ የነበረው ለየት ያለ መልዕክት የሚዘነጋ አልነበረምና!

‹‹...ሀገር ስትቀየር የእኔም ሕይወት እንደሚቀየር ተስፋ ሰጥቶኛል››

የዛሬ 13 ዓመት ለሕዳሴ ግድብ የቦንድ ግዢ እና የገንዘብ ልገሳ ቃል የመግባት መርሐ-ግብር ሚያዝያ 5/2003 ዓ.ም. ኮከብ አዳራሽ ውስጥ ተካሒዶ ነበር፡ ፡ የብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደርን ጨምሮ የሀገር ውስጥ ገቢውን እና ጉምሩክን የሚያስተዳድረው በወቅቱ ስያሜ ‹‹የገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን›› የተሰኘው መ/ቤታችን ሠራተኞች ለግድቡ ግንባታ የሰጡት 16 ሚሊየን 500ሺ ብር ነበር፡፡ ከዚያም በኋላ በተለያዩ መንገዶች ልግስናው ቀጥሏል፡፡

ያኔ የ20 ዓመት ወጣት የነበረው ሳምሶን ግርማ ዛሬ ዕድሜው 33 ደርሶ ሥራውም ከጊዜያዊ የጉልበት ሠራተኛነት በዚያው መደብ ቋሚ፤ ቀጥሎ ደግሞ የጥገና እና የመካኒክ ረዳት ባለሙያነት ደረጃ አድርሶት ነበር፡፡ አሁን ደግሞ በጉምሩክ ኮሚሽን አሽከርካሪ ሆኗል፡፡

የሳምሶን እና የሌሎችም እገዛ ከኢትዮጵያውያን ያላሰለሰ ርብርብ ጋር በራስ አቅም ተጀምሮ የነበረው ግድብ ዛሬ የግንባታው 95 በመቶ ላይ ደርሶ ለመመረቂያው የወራት ብቻ ዕድሜን እየጠበቀ ነው፡፡

የግድቡ እዚህ ደረጃ መድረስ ምን ስሜት እንዳሳደረበት የጠየቅነው ሳምሶን፤ ‹‹የግድቡ እዚህ ደረጃ መድረስ ሀገር ስትቀየር የእኔም ሕይወት እንደሚቀየር ተስፋ ሰጥቶኛል፡፡ ግድቡ በሒደት እዚህ እስኪደርስ እንዳሳየው ዕድገት እኔም በትምህርትም፣ በሥራ ደረጃም፣ በሙያም ሆነ በቤተ-ሰብ ምስረታ የተለወጥሁት ከሀገር ዕድገት ተጠቃሚ በመሆኔ ነው፡፡ በቀጣይ ዓመት ተጠናቆ ሲመረቅ እና ሙሉ በሙሉ ወደ ሥራ ሲገባ የእኔም፣ የሌላውም ዜጋ ሕይወት አሁን ከነበርንበት ቦታ ከፍ ወዳለ ደረጃ እንደሚደርስ እምነት አሳድሮብኛል›› ነው ያለን፡፡

ይህ ግድብ ሊጠናቀቅ ጥቂት ቢቀረውም ማስፈጸሚያው አሁንም ከሕዝብ ስለሚፈለግ የተለመደ ተሳትፎው እንዲቀጥል የግድቡ ግንባታ አስተባባሪ ብሔራዊ ጽ/ቤት ስላሳሰበ ሁላችንም በገንዘባችን እንደጀመርን በገንዘባችን እንጨርሰው፡፡

እንግዶችን

አዘጋጅ:- ሺመልስ ሲሳይ

# « ግብርን በታማኝነት መክፈል በርካታ ጠቀሜታዎች አሉት»

ወ/ሮ ማህሌት አምዴ

**ሚ**ኒስቴር መ/ቤቱ የታክስ ሕግ ተገዢነትን ለማሳደግ በርካታ ተግባራትን በማከናወን ላይ ይገኛል፡፡ በተከናወኑ ተግባራትም አበረታች ውጤቶች የተመዘገቡ ሲሆን መንግስትም ይህንን ስኬት ለማስቀጠል ካለፉት ጥቂት ዓመታት ጀምሮ ለታማኝ ግብር ከፋዮች ዕውቅና እየሰጠ ይገኛል፡፡ እኛም ይህንን እና መሠል ጉዳዮችን አስመልክቶ ከሚኒስቴሩ የሥጋትና ሕግ ተገዢነት ስትራቴጂ ዳይሬክተር ከወ/ሮ ማህሌት አምዴ ጋር ቆይታ አድርገናል፡፡

**የታክስ ሕግ ተገዢነት ማለት ምን ማለት ነው?**

የታክስ ህግ ተገዢነት ማለት የታክስ ባለስልጣኑ የተጣለበትን ሃገራዊ ኃላፊነት ለመወጣት መንግስት ከዚህ ጋር በተያያዘ የሚያወጣቸውን አዋጆች፣ ደንቦች መመሪያዎች እና የአሰራር ስርዓቶችን ተቀብሎ ማከበር፣ ግዴታዎችንና መብቶችን በኃላፊነት፣ በፍቃደኝነት እና በታማኝነት መወጣት ማለት ነው፡፡

**አንድ ግብር ከፋይ ለሕግ ተገዢ ነው የምንለው ምን ምን ጉዳዮችን ሲያሟላ ነው?**

አንድ ግብር ከፋይ የህግ ተገዢ ነው የምንለው አራት መሰረታዊ እና በአለም አቀፍ ደረጃ የሚታወቁ ጉዳዮችን ሲያሟላ ነው፡፡ የመጀመሪያው ጉዳይ በግብር ከፋይነት መመዝገብ /Registration/ ነው፡፡ ከዚህ ጋር ተያያዞ ማንኛውም ግብር ከፋይ የታክስ አስተዳደሩን አስመልክቶ ለውጦች ሲኖሩም ማሣወቅ ይጠበቅበታል፡፡ አንድ ግብር ከፋይ ለመመዝገብ በግብር ከፋይነት ለመመዝገብ በቅድሚያ አሻራ መስጠት፣ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር /TIN/ ማውጣት እንደ አስፈላጊነቱ የሂሳብ መዝገብን መያዝ ይኖርበታል፡፡ ከዚህም በተጓዳኝ ለተጨማሪ እሴት ታክስ፣ ለኤክሳይስ ታክስ እና ለሌሎችም መመዝገብ አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ ሁሉ እንዲመዘገብ ይጠበቃል፡፡

ሁለተኛው ግብርን ማሳወቅ /Filing/ ነው፡፡ ማንኛውም ግብር ከፋይ በህጉ በተቀመጠው የግብር ማሳወቂያ የጊዜ ገደብ መሰረት ግብሩን በታማኝነት በወቅቱ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

ሦስተኛው ሪፖርት የማደረግ ኃላፊነትን መወጣት /Reporting/ ነው፡፡ ይህ ማለት አንድ ግብር ከፋይ ከምዝገባው ጋር በተያያዘ ማሣወቅ የሚገባውን የግብርና ታክስ ማስታወቂያዎች በታማኝነት ሲያስታውቅ ያቀረባቸውን ማስታወቂያዎች /Tax declarations or returns/ ትክክለኛነት ሊያስረዳ የሚችል አስረጂ የሆኑ ሰነዶችን በህጉ አግባብ መያዝ ይጠበቅበታል፡፡ እነዚህን ሰነዶች እንዲያቀርብ ሲጠየቅ በማናቸውም ጊዜ ለታክስ አስተዳደሩ የማቅረብና ትክክለኛነቱን የማስረዳት ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡ ይህ ማለት ግብር ከፋዩ የሚያቀርባቸው ማናቸውም ማስታወቂያዎች /Tax declarations or returns/ መረጃዎች ተጨባጭ እና በወቅቱ መቅረብ አለባቸው ማለት ነው፡፡

አራተኛው ግብርን በወቅቱ መክፈል ሲሆን ከዚህም በተጓዳኝ አንድ ግብር ከፋይ ግብሩን ሲከፍል ተመላሹን በትክክል ስለማቅረቡ፣ በማስታወቂያው ላይ የተመለከቱት ክፍያዎች ሁሉ መካተታቸውን፣ በህግ የተፈቀዱ ኪሳራዎች በአግባቡ መቅረባቸውን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

**ግብር ከፋዮች ለሕግ ተገዢ መሆናቸው ምን ምን ጠቀሜታዎች አሉት?**

በአንድ አገር የታክስ ህግ ተገዥነት መስፈን በርካታ ጠቀሜታዎች አሉት፡፡ ከነዚህ ጠቀሜታዎች መካከል ለግብር ከፋዩ እና ለግብር ሰብሳቢው አካል ብሎም በአጠቃላይ ለሀገራችን ኢኮኖሚያዊ፣ ማሕበራዊና ፖለቲካዊ የተረጋጋ እንዲሆን ያግዛል፡፡

ሌላው ግብር ከፋዮች ለህግ ተገዢ ከሆኑ ተጠቃሚ የሚሆኑት እራሳቸው ናቸው፡፡ ይህንን ተግባራዊ ባደረጉ ቁጥር ከአላስፈላጊ ወጪ ይድናሉ፡፡ ይህም ማለት



ግብራቸውን በታማኝነት አሳውቀው ካልከፈሉ ግብር ከፋዮችና እና አስከፋዩ ወደ አላስፈላጊ ክርክር እና ቅጣት ይገባሉ፡፡ በዚሁም ላላስፈላጊ ወጪ እና የጊዜ ብክነት ይዳረጋሉ፡፡ ከዚህም ባሻገር በታክስ አስተዳደሩ ዘንድ አመኔታን በማጣት የአገልግሎት ጥያቄ ምላሽ ረዘም ያለ ጊዜ ይወስዳል፡፡ በዚህም የገንዘብና የጊዜ ተጎጂ ይሆናሉ፡፡

በሦስተኛ ደረጃ ተጠቃሚ የሚሆነው መንግስት ነው፡፡ ግብር ከፋዮች ለህግ ተገዢ ካልሆኑ መንግስት እነዚህን ግብር ከፋዮች ወደ ህጋዊነት ለማምጣት አስተዳደራዊ ወጪ ያወጣል፡፡ ነገር ግን ግብር ከፋዮቹ ለታክስ ህጉ ተገዢ ከሆኑ መንግስት የሚያወጣው ወጪ በጣም አነስተኛ ይሆናል፡፡ መንግስትም ለዚህ የሚያወጣውን ወጪ ለተጨማሪ ኢንቨስትመንት በማዋል አቅሙን ያሳድጋል ማለት ነው፡፡ ተገቢው ልማት በሚፈለገው ጊዜና ቦታ ተግባራዊ ሲደረግ የዜጐች የአኗኗር ሁኔታ ተቀይሮ የተሻለ አስተሣሰብን በማጐልበት መልካም የሆነ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ አስተዋጽኦ እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡

አራተኛው ጠቀሜታ ለግብር ከፋዮች መልካም ስምን መገንባት ነው፡፡ ግብር ከፋዮች ለታክስ ህግ ተገዢ በሆኑ ቁጥር በየትኛውም ቦታ መልካም ስምን እና አመኔታን ያተርፋሉ፡፡ በዚሁም በመንግስት አገልግሎቶች የተቀላጠፈ መስተንግዶን ያገኛሉ፡፡

**መንግስት ከ2012 ዓ.ም ጀምሮ ለታማኝ ግብር ከፋዮች ዕውቅና ሰርተፍኬት በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡ ታማኝ ግብር ከፋይ ለመሆን ምን ምን ተግባራት መሟላት ይኖርባቸዋል?**

በመጀመሪያ ደረጃ አንድ ግብር ከፋይ ታማኝ ግብር ከፋይ ለመባል ከላይ የተዘረዘሩትን አራት መሠረታዊ የህግ ተገዢነት ጉዳዮችን/ባህሪያትን/ ማሟላት የሚኖርበት ሲሆን እነዚህ እንደተጠበቁ ሆነው በእነዚህ ውስጥ 12 ዝርዝር መመዘኛ መስፈርቶች ላይ የተቀመጡ ነጥቦችን ማሟላት ይጠበቅባቸዋል፡፡ እነዚህም መስፈርቶች መሰረታዊ የግብር ከፋይ መረጃ/ዘርፍ እና የባንክ አካውንትን ጨምሮ፣ ታክስ የማስታወቅ ታሪክ፣ የግብር ከፋዩ የቅጣት ታሪክ፣ የኦዲት ግኝት ልዩነት፣ የግብር/ታክስ ስሌት ልዩነት (Assesment Difference)፣ የተመላሽ ጥያቄ ልዩነት (Refund difference)፣ ግብር ከፋዩ በሁሉም የታክስ ዓይነቶች ያበረከተው የገቢ አስተዋፅዖ፣ ከታክስ ማጭበርበርና ስወራ ጋር በተያያዘ ያለ መረጃ/ታሪክ/፣ የግብር ከፋዩ የእዳ አከፋፈል ታሪክ እና ከእዳ ጋር በተያያዘ ያለበት ሁኔታ፣ ግብር ከፋዩ በጉምሩክ በኩል ያለው የስጋት ደረጃ፣ ግብር ከፋዩ በጉምሩክ የድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት እና የድንገተኛ ፍተሻ ያለው ታሪክ፣ በግብር ከፋዩ ላይ ከፌደራል ፖሊስና ከጠቅላይ ዐቃቤ ህግ የተገኘ የወንጀል መረጃ የሚሉትን ጉዳዩች የያዙ ናቸው፡፡

**ታማኝ ግብር ከፋይ መሆን ምን ምን ጠቀሜታዎች ይኖሩታል?**

ግብርን በታማኝነት መክፈል ኩራት ነው፡፡ አንድ ግብር ከፋይ የሚጠበቅበትን ግብር በታማኝነት ከከፈለ መብቱን እስከጥግ መጠየቅ ይችላል፡፡ ከዚህም ባሻገር ዓለም አንድ መንደር በሆነችበት በዚህ ዘመን በዓለም ዓቀፍ ደረጃ በተለያዩ ጉዳዮች ግብር ከፋዮች መወዳደር ይጠበቅባቸዋል፡፡ በዚህ ውድድር ላይ ቅድሚያ ለማግኘት ግብርን በታማኝነት መክፈል አማራጭ የሌለው ጉዳይ ነው፡፡

አንድ ግብር ከፋይ ግብሩን በታማኝነት በከፈለ ቁጥር ከሚያገኘው የህሊና እርካታና ነፃነት በተጨማሪ መልካም ስምን ያተርፋል፣የተቀላጠፈ አገልግሎት ያገኛል፣ሀብትንና ወጪን በመቆጠብ ብክነትን ያስወግዳል፣ በትክክለኛ መረጃ ላይ የተመሰረተ የግብር አከፋፈል ሁኔታ እንዲኖር ያደርጋል፡፡ በአጠቃላይ ግብርን በታማኝነት መክፈል በመንግስት እና በግብር ከፋዮች መካከል መተማመንን ይፈጥራል፡፡

**ተሻላሚ ግብር ከፋዮችን የሚያበረታታ መመሪያ እየተዘጋጀ ይገኛል፡፡ በመመሪያው መሠረት እነዚህ ግብር ከፋዮች ምን ምን ጠቀሜታዎችን ያገኛሉ?**

ከላይ እንደተጠቀሰው ግብርን በታማኝነት መክፈል ጥቅሙ ለራስ ነው፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ታማኝ ግብር ከፋዮችን ለማበረታታት በመንግስት መመሪያ እየተዘጋጀ ይገኛል፡፡ በዚህ መመሪያ መሠረትም ግብራቸውን በታማኝነት ከፍለው በአገር አቀፍ ደረጃ እውቅናና የምስክር ወረቀት ይሰጣቸዋል፡፡ እነዚህ ግብር ከፋዬች በመንግስት ተቋማት አገልግሎት ፈልገው ሲመጡ ቅድሚያ እንዲሰጣቸው ይደረጋል፡፡ ለምሳሌ በአየር መንገዳችን አገልግሎት ፈልገው ሲመጡ ለነዚህ ግብር ከፋዮች ቅድሚያ የመስተናገድ ዕድል ይመቻችላቸዋል ማለት ነው፡፡ በተመሳሳይም በሌሎች ተቋማትም ይሄው ተግባራዊ የሚደረግ ይሆናል፡፡ አሁን መመሪያው እየተዘጋጀ ስለሆነ ልክ መመሪያው እንደ ጸደቀ ወደ ትግበራ የሚገባና በዝርዝር የሚገለጽ ይሆናል፡፡

**ቀሪ የሚሉት ነገር ካለ**

መንግስት በቀጣይ ዓመታት የሃገር ውስጥ ወጪን በሃገር ውስጥ ገቢና ቀረጥ እንዲሸፈን ውጥን ይዞ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል፡፡ ይህ ውጥን ግቡን ሊመታ የሚችለው ማንኛውም ግብር ከፋይ የሚጠበቅበትን ግብር በወቅቱ አሳውቆ በታማኝነት ሲከፍል ብቻ ነው፡፡ ሌላው ግብርን በወቅቱ አሳውቆ መክፈል የስልጣኔ ማሳያ ነው፡፡

ታዲያ እውነታው ይሄ ሆኖ ሳለ አንዳንድ ግብር ከፋዮች ግብርን በወቅቱ አሳውቆ በታማኝነት ከመክፈል አኳያ መስተካከል ያለባቸው ጉዳዩች አሉ፡፡ በመሆኑም ከመቼውም ጊዜ በላይ ከታክስ ባለስልጣኑ ጋር ተቀራርቦ በመስራት የህግ ግዴታዎችንና መብቶችን በአግባቡ መተግበር ያስፈልጋል፡፡ የሀገራችንን ስልጣኔና ክብር ማስጠበቅ የምንችለው ሁላችንም የታክስ ህጉ እንዲከበር የየበኩላችንን ስንወጣ ነው፡፡

ሌላው ማስተላለፍ የምፈለገው ከታክስ ባለስልጣኑ ውስጥና ውጪ በመሆን ለግል ጥቅማቸው የታክስ ባለስልጣኑን ስምና ስልጣን ያለአግባብ በመጠቀም፣ ትክክለኛ ያልሆነ ግንኙነትን በመፍጠር የተሣሣተ መንገድን ከሚተገብሩና ከሚያሳስቱ ግለሰቦች ግብር ከፋዮች እራሳቸውን እንዲጠብቁ ነው፡፡

በአንድ አላማ እና በእኩል ባልደረባነት መንፈስ በመትመም የምንመኘውን ዘመናዊና ፍትሐዊ የታክስ አስተዳደር በሃገራችን እንዲገነባ ሁሉም የበኩሉን አስተዋጽኦ እንዲወጣ አሳስባለሁ፡፡

# ለግንዛቤዎ

አዘጋጅ- ሰለሞን ወርቁ

# ደረሰኝ አሳትሞ ለመጠቀም የሚሰጥ ፈቃድ እና ኃላፊነት

## ክፍል አንድ

ደረሰኝ በዕቃ ወይም በአገልግሎት ግብይት ላይ ተመሥርቶ ከሻጩ/ አቅራቢው ለገዥው የሚሰጥና ግብይት ስለመፈፀሙ፣ ገንዘብ ስለመሰብሰቡ፣ ዋጋው ስለመከፈሉ ወይም ለወደፊት ለመክፈል ውል መግባቱን የሚያሳይ ሰነድ ነው፡፡

በፌደራል የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 19(4) ታክስ ከፋዮች ደረሰኝ አሳትመው ስለሚጠቀሙበት ሁኔታ፣ የህትመት ድርጅቶችም ደረሰኝ ሲያትሙ ሊያደርጉት ስለሚገባው ጥንቃቄ፣ የደረሰኝ አይነቶች እና ጥቅም ላይ የሚውሉበት ሁኔታ ተደንግጓል።

አዋጁን ለማስፈፀም የታክስ ደረሰኝ አጠቃቀም እና አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 149/2011 ወጥቶ በስራ ላይ ይገኛል፡፡ በዚህ መሠረት፡-

የማንዋል ደረሰኝ ህትመት ፈቃድ ለማግኘት ማሟላት ያለበት ቅድመ ሁኔታ በሚመለከት

1.ማንኛውም የማንዋል ደረሰኝ ለማሳተም የሚፈልግ ታክስ ከፋይ የህትመት ፈቃድ ለማግኘት የሚከተሉትን ቅድመ ሁኔታዎች ማሟላት አለበት፡-

ሀ) በኢንቨስትመንት ሂደት ላይ ያለ እና የንግድ ሥራ ያልጀመረ ሲሆን ከተከፋይ ሒሳብ ላይ ለተቀነሰ ግብር የሚሰጥ ደረሰኝ ለማሳተም የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር እና የኢንቨስትመንት ሰርተፍኬት፣

ለ) ከተከፋይ ሒሳብ ላይ የንግድ ትርፍ ግብር ቀንሰው እንዲያስቀሩ ውክልና የተሰጣቸው ድርጅቶች፣ መ/ቤቶች፣ ወይም ገለሰብ ነጋዴዎች ከተከፋይ ሒሳብ ላይ ለተቀነሰ ግብር የሚሰጥ ደረሰኝ ለማሳተም የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር፣

ሐ) የንግድ ሥራ ፈቃድ ያላወጣና የመደበኛ ሽያጭ ያልጀመረ ሰው የሙከራ ምርት ለመሸጥ ወይም ለግንባታ ሥራ የተረፈ ዕቃ ለመሸጥ የሚያገለግል ደረሰኝ ለማሳተም ከላይ ለተገለጸው በተጨማሪ ምክንያቱን የሚገልጽ ደብዳቤ ማቅረብ ይኖርበታል፣

መ) የንግድ ሥራ ላይ የተሰማራ ታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር እና ህጋዊ የንግድ ሥራ ፈቃድ እና ምዝገባ ሰርተፍኬት፣

ሠ) የተጨማሪ እሴት ታክስ ቀንሶ ገቢ የማድረግ ኃላፊነት የተጣለበት ወኪል የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር ማቅረብ አለበት።

2.በንግድ ስራ ላይ የተሰማራም ሆነ ያልተሰማራ ሰው የሚታተመው ደረሰኝ ላይ የድርጅቱ የንግድ ምልክት (Logo) እንዲካተት ጥያቄ ያቀረበ እንደሆነ ከኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት የንግድ ምልክቱ የተመዘገበበትን ማስረጃ ማቅረብ ይኖርበታል፣

3.ከላይ በተራ ቁጥር 1 ላይ ተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ደረሰኝ ለማሳተም ጥያቄ የሚያቀርበው ሰው በሚታተመው ድረሰኝ ላይ የንግድ ስም እንዲጠቀስ በሚፈልግበት ጊዜ ንግድ ስም ምዝገባ ምስክር ወረቀት ማቅረብ አለበት፣

4.የማንዋል ደረሰኝ ሊይዝ የሚገባውን መረጃ ያከተተ እና ማሳተም የሚፈልገውን የደረሰኝ ብዛት እና አይነት ናሙና በማቅረብ በደረሰኝ ህትመት መጠየቂያ እና መፍቀጃ ቅጽ ላይ በመሙላት ታክስ ለሚከፍልበት ቅ/ጽ/ቤት ማቅረብ አለበት፣

### ማንዋል ደረሰኝ ሲታተም ደረሰኙ ሊይዛቸው የሚገባው ዝርዝር መረጃዎች

1.የማንዋል ሽያጭ ደረሰኝ ሲታተም ቢያንስ የሚከተሉትን መሰረታዊ መረጃዎች ሊይዝ ይገባል።

ሀ) የአቅራቢው ሙሉ ስም ከነአያት፣ አድራሻ፣ የንግድ ስም፣ አስቀድሞ የተመዘገበ እና የታተመ (pre-printed)፣

ለ) የአቅራቢው የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር፣ ታክስ ከፋዩ ለተጨማሪ እሴታ ታክስ የተመዘገበ ከሆነ የምዝገባ ቁጥሩንና ለታክሱ የተመዘገበበትን ቀን፣ አስቀድሞ የተመዘገበ እና የታተመ (pre-printed)፣

ሐ) የደረሰኙ ተከታታይ ቁጥር፣ አስቀድሞ የተመዘገበ እና የታተመ (pre-printed)፣

መ) የገዥው ሙሉ ስም፣ አድራሻና የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር መመዝገቢያ ክፍት ቦታ ያለው፣

ሠ) የተሸጠው ዕቃ ወይም የተሰጠው አገልግሎት አይነትና ገንዘብ መጠን የሚገለጽበት ክፍት ቦታ ያለው፣

ረ) በሽያጭ ፖሊሲ ወይም በውል ምክንያት የተደረገ የሽያጭ ቅናሽ ገንዘብ መጠን የሚገለጽበት ክፍት ቦታ ያለው፣

ሰ) ታክስ በሚከፈልበት ግብይት ላይ የሚከፈለው የተጨማሪ እሴት ታክስ ወይም የተርን ኦቨር ታክስ መጠን የሚገለጽበት ክፍት ቦታ ያለው፣

ሸ) በፊደል እና በአሃዝ የተጻፈ ጠቅላላ የሽያጭ ወይም የግብይት ዋጋ መጠን የሚገለጽበት ክፍት ቦታ ያለው፣

ቀ) ደረሰኙ የተሰጠበት ቀን የሚገለጽበት ክፍት ቦታ፣

በ) ደረሰኙን ያዘጋጀው ወይም ገንዘቡን የተቀበለው ሰራተኛን ስምና ፊርማ የሚሰፍርበት ክፍት ቦታ፣

ተ) የደረሰኝ አታሚው ስም፣ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር፣ ደረሰኙ የታተመበት ቀንና የአታሚው የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ቁጥር እና የአታሚው ስልክ ቁጥር አስቀድሞ የታተመበት (pre-printed)፣


ቸ) የሽያጭ ደረሰኙ እንዲታተም በታክስ ባለስልጣን የተፈቀደለት ደብዳቤ ቁጥርና ቀን አስቀድሞ የታተመበት (pre-printed)።



### የማንዋል ደረሰኝ ህትመት ፈቃድ አሰጣጥ እና አጠቃቀም

1. ከአንድ በላይ በሆኑ ክልሎች ወይም ከተማ አስተዳደሮች የሚነግድ ወይም ቤት የሚያከራይ የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ ግለሰብ ታክስ ከፋይ በእንዳንዱ ክልል ወይም ከተማ አስተዳደር ለሚከናውነው ግብይት የሚሰጠው ደረሰኝ ዋና ምዝገባ ባከናወነበት ክልል ወይም ከተማ አስተዳደር በሚገኘው የታክስ ባለስልጣን ወይም በገቢዎች ሚኒስቴር ብቻ የተፈቀደና በአንድ አታሚ የታተመ መሆን አለበት፣

2. የህትመት ፈቃድ ሰጠው ክልል ዌም ከተማ አስተዳደር ታክስ ባለስልጣን ለታክስ ከፋይ የፈቀደውን የደረሰን ኤነትና ብዛት ታክስ ከፋዩ የንግድ ስራውን የሚሰራባቸው ዌም ቤት ለሚያከራይባቸው ሌሎች ክልሎች ወይም ከተማ አስተዳደሮች መረጃውን በቋሚነት መላክ አለበት፣



3. በስሩ ቅርንጫፎች ያሉት ንግድ ድርጅት ለቅርንጫፎቹ የሚጠቀምበት ታክስ ደረሰኝ ዋና ምዝገባ ባደረገበት ክልል ወይም ከተማ አስተዳደር በሚገኘው ታክስ ባለስልጣን ወይም ገቢዎች ሚኒስቴር ፈቃድ የሚታተም ይሆናል፣

4. ከአንድ በላይ የንግድ ስራ ዘርፍ እና የንግድ አድራሻ ያለው ታክስ ከፋይ በደረሰኙ ላይ ሁሉም ዘርፎች እና አድራሻቸው ተጠቃሎ መታተም ይኖርበታል፣

5. ታክስ ከፋዩ በተለያ ቦታ ለሚገኝ የንግድ ስራ ግብይት ወይም ቤት ኪራይ ገቢ መሰብሰቢያ እንዲውል ተከፋፍሎ የሚሰራጭ የማንዋል ደረሰኝ ጥራዝ ዝርዝር ስርጭት እንደተከናወነ የደረሰኝ ህትመት ፈቃድ ለሰጠው ታክስ ባለስልጣን በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፣

6. የማንዋል ደረሰኝ የህትመት ፈቃድ የሰጠ ክልል ወይም ከተማ አስተዳደር የታክስ ባለስልጣን ወይም ገቢዎች ሚኒስቴር ታክስ ከፋዩ ስለተሰራጨው የማንዋል ደረሰኝ ጥራዝ ዝርዝር ያቀረበለትን መረጃ ታክስ ከፋዩ የንግድ ስራውን ለሚሰራባቸው የፌደራል፣ የክልል ወይም ከተማ አስተዳደር ታክስ ባለስልጣን በቋሚነት መላክ አለበት።

### የኤሌክትሮኒክስ ደረሰኝ አጠቃቀም ፈቃድ አሰጣጥ

1. በሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ መጠቀም የማችል ታክስ ከፋይ ታክስ ባለስልጣኑን በማስፈቀድ የኤሌክትሮኒክስ ደረሰኝ መጠቀም ይችላል።

2. የኤሌክትሮኒክስ ደረሰኝ መጠቀም የሚፈልግ ታክስ ከፋይ በሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ መጠቀም የማይችልበትን አሳማኝ ምክንያት ገልጾ ጥያቄውን ታክስ ለሚከፍልበት የታክስ ባለስልጣን በጽሑፍ ማቅረብ አለበት፣

3. የቀረበው ጥያቄ ተቀባይነት ሲያገኝ የታክስ ባለስልጣኑ ታክስ ከፋዩን የኮምፒውተር ሶፍትዌሩን የሰራውን ሰው ስም፣ ታክስ ከፋዩ መለያ ቁጥር፣ እና ህጋዊ የንግድ ስራ ፈቃድ እንዲቀርብ በማድረግ ጥያቄውን ባቀረበ በ10 ቀናት ውስጥ ውሳኔውን በጽሁፍ መግለጽ ይኖርበታል፤

4. ታክስ ከፋዩ በኤሌክትሮኒክስ ደረሰኝ ለመጠቀም ፈቃድ የሚሰጠው፡-

ሀ) የሚቀርበው ሶፍትዌር በኮምፒውተር ፕሮግራም አማካኝነት የሚታተመው ደረሰኝ ሚኒስቴሩ ባዘጋጀው የደረሰኝ ናሙና ላይ የተመለከቱትን መረጃዎች የሚይዝ ሆኖ ሲገኝ እና፣

ለ) በታክስ መረጃ ጥቅም ላይ የሚውል መረጃ እንደማይቀየር ለማረጋገጥና ተከታታይ የሆነ የደረሰኝ ቁጥር ለማተም በሚያስችል አኳኋን የተዘጋጀ የኮምፒውተር ፕሮግራም መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ ነው።

### የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ የመስጠት ግዴታ

1. ታክስ ከፋዩ የእቃ ወይም የአገልግሎት ሽያጭ ሲያከናውን ለግብይቱ የሽያጭ ደረሰኝ የመቁረጥ ግዴታ አለበት፣

2. ታክስ ከፋዩ ከንግድ ስራው እንቅስቃሴ ውስጥ የተገኘ ሌላ ገቢ ወይም ማንኛውም በገቢ ገንዘብ፣ በቼክ ወይም በባንክ በታክስ ከፋዩ ስም ለተከፈለ ክፍያ የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ መቁረጥ አለበት፣

3. ታክስ ከፋዩ በዱቤ እቃ እና አገልግሎት ግብይት አከናውኖ አስቀድሞ ዱቤ ደረሰኝ የሰጠ ቢሆንም ክፍያ ሲቀበል ግን በዱቤ ደረሰኙ ላይ የተገለጸውን ቁጥር የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ላይ በማወራረስ ለከፋዩ የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ቆርጦ መስጠት አለበት፣

4. የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ ታክስ ከፋይ ከእቃ ወይም ከአገልግሎት አቅርቦት ግብይት ግዥ የቅድሚ ክፍያ (Advance payment) ሲቀበል ተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰን መስጠት ይኖርበታል።

ይቀጥላል > > >

# ማጉፋሊ እና ሙዚቃ...

ከገጽ 1 የዞረ

በቅጽል ስማቸው ‹‹ቡልዶዘር›› እየተባሉ ሲጠሩ የነበሩት ታንዛኒያዊው ጆን ፖምቤ ማጉፉሊ የተወለዱት ከጭሰኛ ቤተሰብ እንደ አውሮፓውያን ዘመን አቆጣጠር በ1959 በሰሜን ምዕራብ ታንዛኒያ ቻቶ በሚባል ቦታ ነው።

እንደማንኛውም ታንዛኒያዊ ትምህርታቸውን ከስር ጀምረው የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በጥሩ ውጤት በማጠናቀቃቸው ዳሬሰላም ዩኒቨርስቲ ገብተዋል፡፡ ከዚያም ኬሚስትሪን እና ሒሳብን በማጥናት በመምህርነት ተመርቀው በእነዚህ የትምህርት ዓይነቶች አስተምረዋል፡፡

ከማስተማር ጎን ለጎን ወደፖለቲካው ዓለምም ያዘነብሉ ነበረና በ1995 በተደረገው ምርጫ ለመጀመሪያ ጊዜ የተወካዮች ምክር ቤት አባል ሆነው ገቡ፡፡ እ.ኤ.አ. በ2000 ደግሞ የካቢኔ ሚኒስትር ሆነው የተሾሙ ሲሆን ከአምስት ዓመታት በኋላ በ2015 ታንዛኒያን በፕሬዝዳንትነት እንዲመሩ ተመረጡ፡፡ በ2020 በተካሔደው ቀጣዩ ምርጫም ሀገራቸውን እንዲመሩ በድጋሚ ተመርጠዋል፡፡

## ሰውዬው፣ ‹‹ቡልዶዘር›› ለምን ተባሉ?

ማጉፉሊ ፕሬዝዳንት ከመሆናቸው በፊት የሥራና ከተማ ልማት ሚኒስትር ነበሩና የመንገድ ሥራ ፕሮጀክትን እንደ ነፍሳቸው በመቁጠር በስፋት ያሠሩ ነበር። ሕዝቡ ይህን ትጋታቸውን ስለተረዳም ለመንገድ ሥራው ከተሰማሩት ማሽኖች መካከል ደጋግሞ ያየው በነበረው ቡልዶዘር፤ ቅጽል ስም ሰጣቸው።

ይህ ቅጽል ስም ግን ኋላ ላይ እየሰፋ ሄዶ መነሻውን ሳተና ሰውየው የመንግሥት ወጪን መቀነስ እና ሙሰኞችን መጠራረግ ስለሚወዱም ነው ተባለ። የአስተዳደር ዘዬአቸው መጠራረግ ስለነበር ስሙ የተስማማቸው ይመስላል።

## ‹‹ኮሮና ቫይረስ ጂኒ ነው!››

ማጉፉሊ ሚዲያ ማስደንበር ይወዳሉ፤ ነጻ ድምጾችን ያፍኑም ነበር። ተቃዋሚዎችንም አሸብረዋል። ሆኖም ሞታቸውን ያጀበው ያ ሳይሆን ለኮሮና ቫይረስ ያሳዩት የነበረው ንቀት ነው። ምናልባት እሱው ይሆን ከዚህ ዓለም ያሰናበታቸው?

ኮሮና ቫይረስ ታንዛኒያ ሲገባ ማጉፉሊ ተበሳጩ። ሕዝቡ ቀን ተሌት እንዲሠራ እንጂ ቤቱ እንዲቀመጥ በፍጹም አይፈልጉም። እናም፤ አንድ መላ ዘየዱ።

‹‹ሕዝቤ ሆይ፤ ለዚህ ቫይረስ ዳትንበርከክ ቤተክርስቲያን ሄደህ ጸልይ እንጂ በፍጹም ቤት አትቀመጥ!›› አሉ። ሕዝቡም ያን አደረገ። ‹‹ኮሮና ጂኒ የሆነ ሰይጣን እንጂ ተህዋሲ አይደለም›› የሚለውን ሐሳብ በሕዝባቸው ውስጥ አሰረጹ። ሳይንስ ግን ሰውየውን ታዘባቸው።

ከሰኔ 2020 ጀምሮ ማጉፉሊ ‹‹አገሬ ታንዛኒያ ከኮቪድ-19 ተህዋሲ ነጻ ነች›› ሲሉ አወጁ። ማስክ (የአፍ እና የአፍንጫ መሸፈኛ ጭምብል ማጥለቅንም ተሳለቁበት። ኮቪድ-19ን ንቀው የዜና ማድመቂያ አደረጉት። በአገራቸው አልበቃ ብሎ ጎረቤት አገሮች የእንቅስቃሴ ገደብ ሲያደርጉ ‹‹የማይረቡ ፈሪዎች›› አሏቸው፤ ለምዕራቡ ዓለም ፕሮፖጋንዳ ተንበርካኪ እንደሆኑ አድርገውም ሳሏቸው።

## ማጉፋሊ እና ሙስና

ማጉፉሊ በ2015 የታንዛኒያ ፕሬዝዳንት ሆነው ቃለ መሀላ ሲፈጽሙ ለታንዛኒያ የሚያስፈልጓት ዓይነት ፕሬዝዳንት ሆነው ነበር የተገኙት። ሙስናን የሚጸየፉና በሥራ የሚያምኑ፤ ቀን ተሌት ቢሠሩ የማይደክማቸውም ሆኑ።

ሙስና ላይ ደግሞ ኋላ ላይ ሕዝቡ በተጨማሪነት እንደሰጣቸው ስያሜ ቡልዶዘራዊነታቸውን አጠናክረው ቀጠሉበት። ውጤት ተኮር የሆኑ ፕሮጀክቶችን ነድፎ የማስፈጸም አቅማቸው ተደነቀላቸው። በዚህ አቋማቸው ለሌሎች የአፍሪካ አገሮችም ምሳሌ መሆን ጀመሩ።

ገና ፕሬዝዳንት ሆነው በተመረጡ በመጀመርያው ቀን የገንዘብ ሚኒስቴር ቢሮ ሄዱ። የገንዘብ ሚኒስቴሩ ሠራተኞች ደግሞ በሥራ ገበታቸው ላይ ተሟልተው አልተገኙም ነበር። ሁኔታው ማጉፉሊን አጠፋቸው። ስለዚህ፤ ይህን በፍጹም እንደማይታገሱ እቅጩን ተናገሩ። በጉብኝታቸውም ጊዜ የተጋለጠው ከሥራ እየቀረ ለደመወዝ ቀን ብቅ የሚለው ነበረና “ጎስት ወርከርስ” እየተባለ ተጠራርጎ እንዲባረር ተደረገ።

ማጉፉሊ የዛቻ ሰው ብቻ አይደሉም፤ የድርጊትም ጭምር እንጂ! እናም፤ ከሥራ የሚቀሩትን ብቻ ሳይሆን ሙሰኛ አለቆችንም ጠራርገዋል። አንዳንድ ጊዜ ታዲያ ሙሰኛ ሹመኞችን የሚያባርሩት ለሌላው መቀጣጫ እንዲሆኑ በሀገሪቱ ብሔራዊ ቴሌቪዥን የቀጥታ ስርጭት ላይ እየታዩ ጭምር ነበር። በዚህ የተነሳ ሀገሬው ያላቸው፣ ‹‹ቡልዶዘር ኑርልን!›› ሲሆን እሳቸውም በዚህ ተበረታትተው ብዙ ታግለዋል።



## በአላስፈላጊ ወጪ ላይ የወሰዱት እርምጃ

ማጉፉሊ ወጪ የሚባል ነገር ያበሳጫው የነበረው ገና ዱሮ ነው። በተለይ፣ ‹‹ላልተገባ ብልጭልጭ ታንዛኒያ ወጪ ማውጣት የለባትም!›› በሚል አቋማቸው በጽኑ ያምኑ ነበር። ምክንያት የሚያስቀምጡትም፣ ‹‹ድሆች ስለሆንን ነው” በማለት ነው።

## ማጉፊሊ በሥራ ዘመቻ

ማጉፉሊ በሥራ ዘመቻዎች በመሳተፍ ሠርተው ያሳዩ መሪም ናቸው፡፡ በዚህ የተነሳ በድምቀት ይከበሩ የነበሩ በርከት ያሉ ክብረ በዓላትን አስቀርተዋል። በ54 ዓመታት የታንዛኒያ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ የነጻነት ቀን እንዳይከበር ያደረጉት እሳቸው ናቸው። ምክንያት ያሉትም፣ ‹‹ቸበርቻቻ አያስፈልግም፤ ሥራ እንጂ››ን ነው። ይህ ሳያበቃቸው መድረክ ላይ ወጥተው፣ ‹‹ሕዝቤ ሆይ፤ ነጻ የምትወጣው የነጻነት በዓልን በማክበር ሳይሆን ተግቶ በመሥራት ነውና እጅህ በሥራ መቁሸሽ አለበት” ሲሉ ጮኹ።

ማጉፉሊ ሕዝቡን ካዘዙ በኋላ በቅንጡ ቤተ-መንግሥታቸው ሳይቀመጡ በዘመቻ ይሳተፉ፤ ሠርተው ያሳዩም ነበር። ሌላው ቀርቶ፤ የቤተ መንግሥታቸውን ደጅ የሚጠርጉት እራሳቸው ነበሩ።

## የማጉፊሊ ወጪ ቅነሳ

ኃላፊዎቻቸው በሕክምና፣ በጉብኝት እና በሆነ ባልሆነው ምክንያት በሕዝብ ገንዘብ ወደ አሜሪካና አውሮፓ ይጓዙ ስለነበር፣ ‹‹አንድ ኃላፊ የውጭ አገር ጉዞ ቢያደርግ ወዮለት!›› ብለው ደነገጉ፤ ተፈጻሚም ሆነ።

ይህ እርምጃቸው በታንዛኒያውያን ዘንድ እጅግ ተወዶላቸው በማኅበራዊ የትስስር መድረክ መነጋገሪያ ከመሆን አልፎ፣ ‹‹ማጉፉሊ ቀጥሎስ ምን ያደርጉ ይሆን?›› የሚል የድረ-ገጽ ሐረግ /Hashtag/ ተፈጥሮም ነበር።

ማጉፉሊ ከአገራቸው ባሻገር በሌሎች አፍሪካውያን ዘንድም ውስጥ ውስጡን አድናቆት ማግኘት ጀማምረውም ነበር። ለምሳሌ፤ በ2017 አንድ እውቅ የኬንያ ፕሮፌሰር በዳሬሰላም ዩነቨርሺቲ ተገኝተው በሰጡት የአደባባይ ዲስኩር፣ ‹‹አፍሪካ አዲስ አስተዳደር ያሻታል›› ካሉ በኋላ ይህ አፍሪካን የሚለውጠውን የአስተዳደር ዘዬም ‹‹ማጉፉሊኬሽን›› ሲሉ ሰይመውታል።

ማጉፉሊ በዚህን ያህል ተጽእኖ መፍጠር ቢችሉም የዲሞክራሲ ጻር ሆነው ነበር የሚታዩት። በዚህ መሠረትም ተቃዋሚን በማሸመድመድ፣ ነቃፊዎቻቸውን ነቅሶ በማሰር እና ነጻ ሚዲያን በማፈን ስማቸው ይነሳ ነበር።



ማጉፉሊ ወደ መጀመሪያው የፕሬዝዳንት ዘመናቸውን በጀመሩ በሁለተኛ ወራቸው የፓርላማ የቀጥታ ሥርጭት እንዳይተላለፍ አገዱ። ያን ጊዜ ሰበብ ያደረጉት ወጪ ቅነሳን ነበር። ተቃዋሚዎች ግን፣ ‹‹ይህ ነገር ለሳንሱር እንዲመች አድርጎ የፓርላማ ክርክርን ለሕዝብ ላለማቅረብ ነው›› ብለው ከሰሷቸው። እንዲያውም ‹‹ይህን እርምጃ ተቃውመን ሰልፍ እንወጣለን!›› አሉ። ሆኖም ሰልፉ በማጉፉሊ ሰዎች እውቅና ተነፈገውና ታገደ።

## የማጉፋሊ ተፎካካሪ

በ2017 ደግሞ ዋንኛ ተቃዋሚያቸውና የምክር ቤት አባሉ ቱንዱ ሊሱ ቤታቸው ሳሉ ተተኮሰባቸውና ክፉኛ ቆሰሉ። ይህን ያደርጋሉ ተብለው የተጠረጠሩት የማጉፉሊ ሰዎች ናቸው። ሆኖም ሰውየው እንደምንም ድነው ከሦስት ዓመታት በኋላ ተፎካካሪያቸው ሆነው ለፕሬዚዳንትነት ተወዳደሩ።

ሚስተር ሊሱ የግድያ ሙከራ እንደተረገባቸውና ታንዛኒያን እየመሯት ያሉት ሰው አምባገነን እንደሆኑ በተደጋጋሚ ይናገሩ ነበር። በዚህ ንግግራቸው ‹‹ማጉፉሊ እስከወዲያኛው ያሰናብቷቸዋል›› ቢባልም ተፎካካሪያቸው እንዲሆን ፈቀዱላቸው።

ማጉፉሊ የአስተዳደር ዘይቤያቸውን የተጠቀሙት ታንዛኒያውያን ‹‹የነጻነት አባት›› ይሏቸው ከነበሩት ከቀድሞው ፕሬዚዳንታቸው ከጁሊየስ ኔሬሬ ነው

## የማጉፋሊ ምዕራብ ጠልነት

ማጉፉሊ፤ ‹‹ምዕራባዊያን አፍሪካን በዝብዘዋታል›› ብለው ስለሚያምኑ፣ ‹‹በተራችን እነሱን መበዝበዝ አለብን!›› ይሉ ነበር። በዚህ ረገድ በየጊዜው የውጭ ድርጅቶችን የሚያስጨንቁ አዳዲስ መመሪያዎችን ያወጡ ነበር። ከነዚህ መሐል የካናዳው ባሪክ ወርቅ እህት ኩባንያ የሆነውን አካሺያ ማዕድን ድርጅት፣ ‹‹190 ቢሊዮን ዶላር ለመንግሥት ክፈል›› ብለው ይጠይቁታል። እርሱም፣ ‹‹ለምንድነው የምከፍለው?›› ቢላቸው፣ ‹‹በቃ፤ እስከዛሬ የከበሩ ማዕድናትን ከታንዛኒያ ስታወጣ ነበር። ገቢህን ስንደምረው ታንዛኒያ ይህን ያህል ማግኘት እንዳለባት ደረስንበት›› አሉት።

ኩባንያው በሁነታው ተደናግጦ ከብዙ ድርድር በኋላ 300 ሚሊዮን ዶላር ለመክፈል ተስማማ። ከዚህ በኋላም ኩባንያው ከሚያወጣቸው ማዕድናት 50 ከመቶውን ለመንግሥት ገቢ እንዲያደርግ ተገደደ።

ማጉፉሊ የአስተዳደር ዘይቤያቸው የተቀዳው ከአገሪቱ የነጻነት አባት ጁሊየስ ኔሬሬ እንደሆነ ይነገራል። እሳቸውም ይህንን ብለውት ያውቃሉ። ማንም እንዴት አገሬን መምራት እንዳለብኝ ሊነግረኝ አይገባም ይሉ ነበር።

## ‹‹ድህነት ምን ማለት እንደሆነ አውቀዋለሁ››

እሳቸው ልጅ እያሉ ታንዛኒያን የሚያስተዳድሯት ጁሊየስ ኔሬሬ ነበሩ። ‹‹ቤታችን ከጭቃ ነበር የተሠራው፡ ፡ በልጅነቴ ከብቶችን አግድ ነበር። ቤተሰቤን ለመታደግ ወተትና ዓሳ እያዞርኩም እሸጥ ነበር። ድህነት ምን ማለት እንደሆነ ለእኔ አትነግሩኝም፡፡ ለዚህ ነው ድሆችን ለማገዝ ፖለቲካ ውስጥ የገባሁት›› ሲሉም ተናግረዋል።

እነዚህ ሁለ-ገቡ ሰው ያመኑበትን አድርገው እና በቻሉት መጠን ሀገራቸውን በመሪነት አገልግለው ከቆዩ በኋላ በተወለዱ በ61 ዓመታቸው አርፈዋል።

ምንጭ፡- https://www.bbc.com/amharic/news-56439789

# በሚሊዮን የሚቆጠር ብር ወጪ ለማዳን




**በሺመልስ ሲሳይ**

መንግሥት ለቢሮ ኪራይ በየዓመቱ በቢሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ ያወጣል፡፡ ይህም ሃገሪቱ በአሁኑ ወቅት እያከናወነች ካለችው ታላላቅ ፕሮጀክቶች ጋር ተደማምሮ በሃገሪቱ ኢኮኖሚ ላይ ጫና እየፈጠረ ይገኛል፡፡ ይህንንም ችግር በዘላቂነት ለመቅረፍ የመንግሥት መ/ቤቶች የራሳቸው ሕንጻ እንዲኖራቸው በመንግሥት ከተወሰነ በኋላ በርካታ ተቋማት ሕንጻቸውን በመገንባት ላይ ይገኛሉ፡፡

ከነዚህ የመንግሥት ተቋማት መካከል የገቢዎች ሚኒስቴር የዋናው መ/ቤቱን ሕንጻ እድሳት ካደረገ ዓመታት ያስቆጠረ እና አሁንም በማደስ ላይ የሚገኝ ሲሆን ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ደግሞ በኪራይ የያዘዋቸውን ጽ/ቤቶች ትተው በራሳቸው ሕንጻ አገልግሎት ለመስጠት ሕንጻዎቻቸውን በተለያዩ የግንባታ ደረጃዎች ላይ አድርሰዋል፡፡


## 1. የድሬዳዋ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት

ቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ በራሱ ሕንጻ አገልግሎት እየሰጠ ቢሆንም አሁን አገልግሎት እየሰጠበት የሚገኘው ሕንጻ ለተገልጋዮች ምቹ አይደለም፡፡ ስለዚህ እድሳቱን ለመጀመር የሚያስችል የዲዛይን ሥራ ተጠናቆ የግንባታው ግዥ በሒደት ላይ ይገኛል፡፡



## 2. የአዳማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት

አንድ ምድር ቤት እና ስድስት ፎቅ የሚኖረው የቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ አዲስ ሕንጻ ግንባታ የተጀመረ ሲሆን የግንባታ ፕሮጀክቱ አሁናዊ አፈጻጸም 77.63 በመቶ ደርሷል፡፡



## 3. የሐዋሳ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት

በተከራየው ሕንጻ ላይ አገልግሎት እየሰጠ የሚገኘው ቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ምቹ የሥራ ሁኔታን ለማስፈን የሚያስችለውንና አንድ ምድር ቤት እና ስድስት ፎቅ የሚኖረውን ሕንጻ እያስገነባ ሲሆን አፈጻጸሙም 69.91 በመቶ ደርሷል፡፡



## 4. የባህርዳር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት

የዚህ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት አንድ ምድር ቤት እና ባለስምንት ፎቅ የሚይዘው የሕንጻ ግንባታ በአግባቡ እየተከናወነ ቢሆንም በክልሉ የተፈጠረውን አለመረጋጋት ተከትሎ ግንባታው መጠነኛ መጓተት ገጥሞት ሒደቱ 61.2 ሆኗል።




## 5. መቀሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት

ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ አንድ ምድር ቤት እና ስምንት ፎቅ የያዘ አዲስ የሕንጻ ግንባታ ቢጀመርም የሰሜኑን ጦርነት ተከትሎ የግንባታው ሒደት 16.02 በመቶ ላይ እያለ ሙሉ በሙሉ ተቋርጦ ነበር፡፡ ከሠላም መፈጠር በኋላ ግንባታው ቀጥሎ 19.51 በመቶ ላይ ደርሷል፡፡

## 6. የጅማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት

አንድ ምድር ቤት እና ስምንት ፎቅ የሚኖረው የዚህ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የሕንጻ ግንባታ በተለያዩ ወስጣዊ እና ውጫዊ ችግሮች የተነሳ ተጓትቶ አፈጻጸሙ 27.68 በመቶ ላይ ነው፡፡



## 7. የኮምቦልቻ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት

የቅርንጫፍ ጽ/ቤቱን ሕንጻ ግንባታ ፕሮጀክት ለማካሄድ ዕቅድ የተያዘ ቢሆንም ከቦታ ጋር ተያይዞ ያላለቁ ጉዳዮች ሲጠናቀቁ የዲዛይን ሥራው ተከናውኖ ወደ ሥራ ይገባል፡፡

## 8. የከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅርንጫፍ ጽ/ቤት

አራት የምድር ቤት እና 19 ፎቅ የሚኖረው የቅርንጫፍ ጽ/ቤቱን ሕንጻ ግንባታ ለመጀመር የሚያስችል የዲዛይን ሥራው ተጠናቆ የግንባታውን ሂደት ለማስጀመር የሚያስችል የግዢ ሒደት በመፈጸም ላይ ይገኛል፡፡

## 9. የምእራብ አዲስ አበባ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅርንጫፍ ጽ/ቤት

አሁን በኪራይ በያዘው ሕንጻ ላይ አገልግሎት እየሰጠ ቢገኝም ግሎባል ሆቴል አካባቢ የሚገኘው የቀድሞው ቢሮው ታድሶለት እንዲገባ የዲዛይን ሥራ እየተሠራ ይገኛል፡፡

## 10. የሰሜን ምእራብ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅርንጫፍ ጽ/ቤት

ልደታ አካባቢ በሚገኘውና በኪራይ በያዘው ሕንጻ አገልግሎት እየሰጠ የሚገኘው ቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ እንደሌሎቹ የራሱ ሕንጻ እንዲኖረው አዲስ ሕንጻ የግንባታ ዲዛይን እየተዘጋጀለት ይገኛል፡፡

በመግቢያችን እንደጠቆምነው፤ መ/ቤቱ ለሕንጻ ኪራይ እያወያ የሚገኘውን ከፍተኛ ወጪ ለማስቀረት በግንባታ ክፍተቶች ላይ ያሉትን አስተካክሎ ለግንባታ እና ለዕድሳት ፕሮጀክቶቹ አፈጻጸም ሁሉም ባለድርሻ አካላት ሚናቸውን እንዲወጡ እናሳስባለን፡፡

# Tips

BY SHIMELIS SISAY

# It is time to tax the rich... and their foundations

Philanthropic endowments are designed to protect the financial interests of the 1 percent. They should be taxed. We are wrapping up yet another tumultuous year in which wars and disasters have ravaged communities across the world. These misfortunes have added to the misery of those who are already facing the ravages of harsh inequality, climate chaos, dispossession, and marginalization.

As in the past, part of the global response to these crises included the "generous giving" of various philanthropists. Indeed, their representatives joined heads of state, CEOs, celebrities, royalty, and government officials for the annual United Nations General Assembly in September and then for the UN climate conference (COP28) in November to seek "solutions". Many of them will meet again for the World Economic Forum in Swiitzerland/Davos later in January under the same guise.

Yet, every year, nothing seems to change as the outcome of these events. This is partly because the very way elites see problems and solutions is limited by their gaze and worldview, which create and perpetuate the crises in the first place. But they are also ineffective because that is their purpose: They are structured to uphold the status quo, not to create deep systemic change.

The philanthropic sector was also not created to address the root causes of systemic problems, but to protect private financial interests.

It is time for the world to realize this. The sooner we do so, the sooner we can find more relevant ways to truly bring philanthropy into the important and messy work of real social change.

## How the rich get richer

We all know the rich are getting richer, controlling a huge percentage of wealth across the planet. According to Oxfam's recent Global Wealth Inequality Report, since 2020, the richest 1 percent have captured almost two-thirds of all new wealth, nearly twice as much as the bottom 99 percent of humanity.

Rich people pay virtually no tax (often 3 percent or less of their income) and their billions just keep on growing through the application of compound interest. In the next 20 years, most of this wealth will move between family members in the wealthiest 1 percent. In the US alone, it is estimated that between $36 trillion and $70 trillion in wealth will be transferred from one generation to another.




Calls to tax the rich are growing globally and will be even more pronounced as this massive generational wealth transfer takes place. One of the key ways the rich address this pressure is through philanthropy. Philanthropic contributions are commended and perceived as a form of "giving back".

Currently, the estimated global value of philanthropy is $2.3 trillion, or approximately 2 percent of the world's GDP, with most of those funds held in endowments. This is larger than the annual GDP of countries like Canada and Brazil.

If philanthropy is inherently good, and more philanthropy is going to happen, what is there to worry about? Let us look at how philanthropy works in practice.

For example, in the US, one aspect of philanthropy is the 5 percent payout rule which was put into US tax law in 1976. According to these legal provisions, a charitable foundation has to give just 5 percent of its overall endowment in the form of grants or program-related investments annually to maintain its not-for-profit status.

In practice, this rule has become the ceiling for giving grants rather than the floor. The other 95 percent of the endowment is treated as tax-exempt investment money, which most foundations continually grow.

Let us break this down further. In 2020, the average rate of return for foundation endowments was 13.1 percent. If we take a $100m foundation as an example, it would be required to give away just $5m over the year, but its endowment would have grown to $113m minus $5m for a year-end sum of $108m. The following year, this expanded pie of $108m would become $122m minus roughly $5.4m it would give away for a total of roughly $117m. So, the $100m becomes $117m in just two years and continues to grow.

These endowment funds – or rather untaxed investment capital – are then funneled into the usual engines of extractive capitalism: stock markets, bonds, real estate, fossil fuel companies, etc. This results in further wealth accumulation.

While this 5 percent rule payout started in the US, it has been exported around the world and continues to be promoted as the global model for philanthropy: keep growing endowments, while foundations grant the minimum amount required. Their wealth and power grow while they trickle-down grants to those doing the hard work.

## Pipe

It does not take an accountant or an economist to understand the implications of this model. Only a fraction of tax-exempt philanthropic funding is used to address social and ecological issues while the majority is reinvested in life-destroying activities via the extractive markets with high, ongoing returns on investment.

## Philanthropy as redistribution

In most countries, any individual or corporation that makes a philanthropic donation receives a direct tax break against their income for the donated amount. As a result, philanthropy is an important part of a larger tax minimization strategy, further concentrating wealth.

A recent investigative report by The Nation magazine estimated that Bill Gates may have received more money back in the form of tax breaks than he has given in philanthropic grants through the activities of the Gates Foundation.

Another example involves MacKenzie Scott, one of the largest philanthropic donors in the US. Over the past couple of years, she has been celebrated for the size, type, and speed of her grants. According to Bloomberg's Billionaire Index, in 2023, her wealth continued to grow, even though she gave away significant funds.

Despite receiving huge tax benefits and doling out the smallest fraction of their endowments as grants, philanthropists are elevated in our society as benevolent, generous, and magnanimous individuals.

It is time to drop the hero worship of philanthropists and go beyond simple declarations to tax the rich. We need to start taxing endowments.

Consider what a tax on these massive philanthropic endowments could do. For example, democratically run citizens' funds created with the proceeds from taxing endowments could redistribute billions of dollars to front-line communities, Indigenous peoples, climate refugees, and even ecologies who have suffered the most from the extraction of resources and wealth.

This can be the starting place for deeper structural change in philanthropy. What is needed is nothing short of a shift in worldview, a commensurate alternative approach based on a life-centric economy, and a genuine desire to address the global poly-crisis.

It is time to move from systems protecting individual and institutional entitlements to ones that are rooted in redistributing wealth for the collective entrustment of futures worth living.

The views expressed in this article are the author's own and do not necessarily reflect Al Jazeera's editorial stance.

***Source**:- Aljazeera*

ሕገ-ግብር

አዘጋጅ፡- ሰሎሞን ወርቁ

# ያልተከፈለ ታክስ እና አስተዳደራዊ ቅጣት

(ካለፈው የቀጠለ)

## ከተከፋይ ሒሳብ ላይ ተቀንሶ ከሚከፈል ግብር ጋር በተገኘ የሚጣል ቅጣት

1. ከተከፋይ ሒሳብ ላይ ግብር ቀንሶ ባለመክፈል በአዋጁ አንቀጽ 106 ንዑስ አንቀጽ 2 እና 3 መሠረት የሚጣለው ቅጣት ተፈፃሚ የሚሆነው ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ተቀንሶ ቀሪው ገንዘብ በታክስ መክፈያ ጊዜ ባለመክፈለ ይሆናል።

በአዋጁ አንቀጽ 106 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት “ የሚጣለው ቅጣት መጠን ከዋናው የታክስ ዕዳ መብለጥ የለበትም።” የሚል ሲሆን ንዑስ አንቀጽ 3 ደግሞ “መክፈል በማይገባው ታክስ ላይ ሳይከፈል በዘገየበት የተጣለ ቅጣት በአዋጁ አንቀጽ 4 መሰረት ለታክስ ከፋዩ ይመለሳል።” ይላል።

2. በአዋጁ አንቀጽ 106) ንኡስ አንቀጽ 2 መሰረት ግብር ቀንሶ ገቢ ያደረገ የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ እና ዋና ሒሳብ ሹም ወይም ዋና ሂሳብ ሹም የሌለ እንደሆነ ታክስ ቀንሶ መያዝ እንዳለበትና የተያዘውም ታክስ መከፈል እንዳለበት የማረጋገጥ ኃላፊነት ያለበት ማንኛውም ሌላ የድርጅቱ ሠራተኛ በእያንዳንዱ የታክስ መክፈያ ጊዜ ተቀንሶ ገቢ ላልተደረገ ግብር እያንዳንዳቸው ብር 2000 ቅጣት ይከፍላሉ፣

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገው ቢኖርም አንድ ሰው ከአንድ በላይ ኃላፊነቶች ደርቦ የሚሠራ ከሆነ የሚጣለው ቅጣት ተፈፃሚ የሚሆነው እንደ አንድ ኃላፊ ብቻ ይሆናል፤

4. በአዋጁ አንቀጽ 106 ንዑስ አንቀጽ 3 የተጣለው ቅጣት ተፈጻሚ የሚሆነው የገቢ ግብር አዋጅ አንቀጽ 92 (3) ተፈጻሚ በሚደረግባቸው ገዢ እና አቅራቢ ላይ ነው።

## ደረሰኝ ባለመስጠት ወይም ትክክለኛ ያልሆነ ደረሰኝ በመስጠት የሚጣል ቅጣት

1. አዋጁ አንቀጽ 108 መሠረት ደረሰኝ መስጠት ሲገባው ያልሰጠ ማንኛውም ታክስ ከፋይ ለገዥው ባልሰጠው ለእያንዳንዱ ግብይት ብር 50,000 ይቀጣል። ይህ ድንጋጌ ማንዋል ደረሰኝ ወይም የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ተጠቃሚ የሆነ ታክስ ከፋይ ላይ ሁሉ ተፈጻሚ ይሆናል።

2. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌ ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ለሚቀነስ ግብር የሚሰጥ ደረሰኝን በሚመለከት ተፈጻሚ አይሆንም።

## ታክስ አሳንሶ በማስታወቅ የሚጣል ቅጣት

በአዋጁ አንቀጽ 109 መሠረት የጣለው ቅጣት ጥፋቱ ለመጀመሪያ ጊዜ፣ ለሁለተኛ ጊዜ፣ ለሶስተኛ ጊዜ፣ እና ከዚያ በላይ የተፈፀመ በሚሆንበት ጊዜ የተለያየ ሲሆን የጥፋቱ መጠን የሚቆጠረው አዋጁ ተፈጻሚ መሆን ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ለየታክስ ዓይነቱ ተለያይቶ እና የታክስ ስሌት ውሳኔው በአንድ ጊዜ የተወሰነ ቢሆንም ጥፋት በተገኘባቸው የታክስ ማስታወቂያዎች ብዛት ነው።

በአዋጁ አንቀጽ 109 መሰረት ታክስን አሳንሶ ማሳወቅ የሚያስከትለው ቅጣት፡-

1/ በታክስ ማስታወቂያ የተገለጸው የታክስ መጠን ታክስ ከፋዩ ሊከፍል ከሚገባው ትክክለኛ የታክስ መጠን ያነሰ እንደሆነ (ልዩነቱ “የታክስ ጉድለት” ተብሎ የሚገለጽ) የታክስ ጉድለቱን መጠን 10% (አሥር በመቶ) ቅጣት ይከፍላል።

2/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በታክስ ከፋዩ ላይ ለሁለተኛ ጊዜ ተፈጻሚ በሚሆንበት ጊዜ የቅጣቱ መጠን ወደ 30% (ሰላሳ በመቶ) ከፍ ይላል።


የገንዘብ ሚኒስቴር

የአስተዳደራዊ ቅጣት አወሳሰን

መመሪያ

ገንዘብ ሚኒስቴር

ጳጉሜ 2011 ዓ.ም

3/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በታክስ ከፋዩ ላይ ለሦስተኛ ጊዜ እና ከዚያ በላይ ተፈጻሚ በሚሆንበት ጊዜ የቅጣቱ መጠን ወደ 40% (አርባ በመቶ) ከፍ ይላል።

4/ የታክስ ጉድለቱ የተፈጠረው ታክስ ከፋዩ የራሱን ታክስ አስልቶ የታክስ ማስታወቂያ ከማቅረቡ በፊት ሚኒስቴሩ ማብራሪያ ባልሰጠበት አከራካሪ በሆነ የታክስ ሕግ ድንጋጌ ላይ በያዘው ምክንያታዊ አቋም ላይ የተመሠረተ ሆኖ ከተገኘ በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚጣል ቅጣት ተፈጻሚ አይሆንም።

## ታክስን በመሸሽ የሚጣል ቅጣት

በአዋጁ አንቀጽ 110 የተጣለው ቅጣት በገቢ ግብር አዋጅ አንቀጽ 78 እስከ 80 እና በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ አንቀጽ 60 ታክስን መሸሽን ለመከላከል የሚያስችል ድንጋጌዎች በመተላለፉ በተፈፀሙ ድርጊቶች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

በአዋጁ አንቀጽ 110 መሰረት ባለሥልጣኑ የታክስ ከፋይን የታክስ ስሌት ሲሠራ ከታክስ መሸሽን የሚከላከል ድንጋጌ ተፈጻሚ ካደረገ ታክስ ከፋዩ ይህ ድንጋጌ ተፈጻሚ ባይደረግ ኖሮ ከታክስ በመሸሽ ሊያስቀር ይችል የነበረውን የታክስ መጠን እጥፍ ቅጣት ይከፍላል።

## የታክስ ማስታወቂያና መክፈያ ጊዜ

1. አንድ ታክስ ከፋይ ታክስ ያስታወቀበት እና የከፈለበት ጊዜ የተለያየ ከሆነ ታክስ ባለማስታወቅ እና ታክስ ባለመክፈል የሚጣል ቅጣት የዘገየውን ጊዜ መሠረት በማድረግ ተለያይቶ መወሰን አለበት።

2. ታክስ ከፋይ ሊከፍል የሚገባውን ታክስ ወደ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የባንክ ሂሳብ ገቢ ያደረገ ቢሆንም የታክስ ማስታወቂያ በወቅቱ ሳያቀርብ ያዘገየ ከሆነ ቅጣት የሚጣልበት በአዋጁ አንቀጽ 104 ድንጋጌ መሠረት የታክስ ማስታወቂያ ባለማቅረብ ወይም ዘግይቶ በማቅረብ ብቻ ይሆናል።

ታክስ ከተወሰነ በኋላ ባልተከፈለው ታክስ ላይ የሚወሰን ቅጣት

1. አንድ ታክስ ከፋይ የታክስ ውሳኔ በተሰጠው በ30 ቀን ውስጥ ታክሱን ከከፈለ በአዋጁ አንቀጽ 37 (8) በተደነገገው መሠረት ወለድ የማይታሰብበት ሲሆን፣ በተመሳሳይ የአስተዳደራዊ ቅጣትም ተፈጻሚ አይደረግበትም።

በአዋጁ አንቀጽ 37 ንዑስ አንቀጽ 8 መሰረት፡-

ሀ) ባለሥልጣኑ በታክስ ሕግ መሠረት ከታክስ ከፋዩ የሚፈለገውን የታክስ ዕዳ የታክስ ስሌት ማስታወቂያን ጨምሮ በማንኛውም የጽሑፍ ማስታወቂያ ያሳወቀው እንደሆነ፤ እና

ለ) ታክስ ከፋዩ ማስታወቂያው እስከተሰጠበት ቀን ድረስ መክፈል የሚጠበቅበትን የዘገየ ክፍያ ወለድ ጨምሮ በማስታወቂያው የተመለከተውን የታክስ ዕዳ በሙሉ በማስታወቂያው በተገለጸው የመክፈያ ቀን የከፈለ ከሆነ ማስታወቂያው በተሰጠበት እና ክፍያው በተፈጸመበት መካከል ላለው ጊዜ የዘገየ ክፍያ ወለድ አይታሰብም።

2. ታክስ ከፋዩ በቅሬታ እና በይግባኝ በቆየበት ጊዜ ባልተከፈለ ታክስ ላይ አስተዳደራዊ ቅጣት ይቀጣል። ይህ ተፈጻሚ የሚሆነው በቅሬታ እና በይግባኙ ውሳኔ መሠረት በግብር ከፋይ ላይ በሚፀናው የግብር መጠን ልክ ይሆናል።

## መረጃ ያለመስጠት የሚያስከትለው ቅጣት

ማናቸውም መረጃ የመስጠት ግዴታ ያለበት ሰው ሚኒስቴሩ በአዋጁ አንቀጽ 65 መሠረት በጽሁፍ ማስታወቂያ ሲጠይቀው በጽሁፍ በማስታወቂያው በተጠቀሰው ቦታ እና ጊዜ የተጠየቀውን መረጃ ያላቀረበ እንደሆነ መረጃውን ያልሰጠው ሰው ወይም መረጃ የተጠየቀው መ/ቤት የበላይ ኃላፊ በአዋጁ አንቀጽ 114 (7) በተደነገገው መሠረት

5000 ብር ቅጣት ይጣልበታል።

በታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁትር 983 2008 አንቀጽ 65 መሰረት መረጃ ወይም ማስረጃ ለማግኘት ማስታወቂያ መስጠትን በተመለከተ፡-

1. ማንኛውንም የታክስ ሕግ ለማስተዳደር ሲባል ባለሥልጣኑ ታክስ ከፋይ ቢሆንም ባይሆንም ለማንኛውም ሰው የጽሑፍ ማስታወቂያ በመስጠት፡-

ሀ) በማስታወቂያው በተመለከተው ጊዜ ውስጥ የራሱን ወይም የሌላ ማንኛውንም ሰው የታክስ ጉዳይ የሚመለከት በማስታወቂያው የተገለፀውን መረጃ እንዲሰጠው፤

ለ) በማስታወቂያው በተመለከተው ጊዜና ቦታ በመገኘት የራሱን ወይም የሌላ ማንኛውንም ሰው የታክስ ጉዳዮች በተመለከተ በማስታወቂያው የተገለጸውን ማስረጃ እንዲሰጠው፤

ሐ) በማስታወቂያው በተመለከተው ጊዜ ከእርሱ ወይም ከሌላ ማንኛውም ሰው የታክስ ጉዳዮች ጋር የሚገናኙ በእጁ ወይም በእርሱ ቁጥጥር ሥር ያሉ በማስታወቂያው የተገለፁ ሰነዶችን እንዲያቀርብ፤ ሊጠይቅ ይችላል።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት እንዲቀርብ የተጠየቀው ሰነድ ከሆነ፣ የተጠየቀው ሰነድ መለየት በሚያስችል አኳኋን በማስታወቂያው መገለጹ በቂ ይሆናል።

3. ይህ አንቀጽ፡- ሀ) በኤሌክትሮኒክ መልክ የሚገኙትን ጨምሮ ማንኛውንም መረጃ መስጠትን ወይም ሰነድ ማቅረብን በተመለከተ ልዩ መብት የሚሰጥ ወይም የህዝብ ጥቅምን የሚመለከት ሌላ ሕግ ፤ወይም

ለ) ሚስጥር የመጠበቅ ግዴታን የሚጥል ውል፤ ቢኖርም ተፈጻሚ ይሆናል።

## ስለቅጣት አወሳሰን

1. የገቢዎች ሚኒስቴር የሚወስነው አስተዳሰደራዊ ቅጣት የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ በመስጠት የሚፈጸም ይሆናል።

2. አንድ ድርጊት መፈጸም ወይም ያለመፈጸም የሚያስከትለው ቅጣት በአንድ ታክስ ብቻ ያልተወሰነ ሲሆን እያንዳንዱ ቅጣት ለየብቻ ከተወሰነ በኋላ ሁሉም ቅጣቶች ተጠቃለው ይጣላሉ። ይህ ተፈጻሚ የሚሆነው በተለያዩ የታክስ ዓይነቶች ለሚፈጸሙ የሚከተሉት ጥፋቶች ብቻ ነው።

ሀ) ሰነድ ባለመያዝ፣

ለ) ታክስ በጊዜው ባለማስታወቅ፣

ሐ) ታክስ ዘግይቶ መክፈል፣

መ) ታክስ አሳንሶ ማስታወቅ፣

ሠ) ታክስን መሸሽ፣

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተመለከተው አንድን ታክስ በሚመለከት ታክስ ከፋዩ የተለያዩ ድንጋጌዎች የጣሰ በሚሆንበት ጊዜ ተፈጻሚ ይሆናል።

ማስታወቂያ




የገቢዎች ሚኒስቴር ራዕይ

በ2022 ዘመናዊ የታክስ አስተዳደር ተገንብቶ ሀገራዊ ወጪ በታክስ ገቢ ተሸፍኖ ማየት

እ ሴ ቶ ች

1. አገልጋይነት (Customer centric)
2. ሙያዊ ብቃት (Professionalism)
3. በቡድን መሥራት (Team work)
4. መሰጠት (Dedication/commitment)
5. ታማኝነት (Loyality)